# ዋና ፀሐፊ ከፌዴራል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተወካይ ጋር በሁለትዮሽ ግንኙነት ዙሪያ ተወያዩ

የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ፀሐፊ እንዳልካቸው ስሜ ታህሣሥ 17 ቀን 2010 ዓ.ም. በፌዴራል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የቻይና ጓንዡ ግዛት የቢዝነስ ዲፕሎማሲ ዳይሬክተር ጀነራል አቶ ተፈሪ መለሰን በጽ/ቤታቸው ተቀብለው አነጋገሩ፡፡ ሁለቱ ኃላፊዎች ምክር ቤቱና ዳይሬክቶሬት ጄኔራሉ በጋራ ሊሠሩ በሚችሉባቸው ጉዳዮች ላይም ተወያይተዋል፡፡



ከላይ ከቀኝ ወደ ግራ፡- አቶ እንዳልካቸው ስሜ እና አቶ ተፈሪ መለሰ

አቶ እንዳልካቸው በተለይ ንግድና ኢንቨስትመንትን ከማስፋፋት ጋር በተያያዘ ወቅታዊ መረጃዎችን በመለዋወጡ ረገድ መሥራት እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መረጃዎች በሚላኩበት ወቅት መዘግየቶች እንዳይታዩ ትኩረት ተሰጥቶ ቢሠራም የተሻለ እንደሚሆን አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

ምክር ቤቱ በቀጣይ የምክር ቤቱን ማዕከል ለማስገንባት ማቀዱን ያስታወሱት ዋና ፀሐፊው ለፕሮጀክቱ ግንባታ ተባባሪ ቻይናውያንን በማፈላለግ ዳይሬክቶሬት ጄኔራሉ በቅርበት ለመነጋገር ጥረት እንዲያደርግም ጠይቀዋል፡፡ ምክር ቤቱ በየዓመቱ የሚያካሂደውን ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒትና የሚያወጣቸውን ህትመቶችም በግዛቲቱ በማስተዋወቁና እ.ኤ.አ. በ2021 ኢትዮጵያ የምታስተናግደውን 12ኛውን የዓለም ምክር ቤት ኮንግረስ (World Chamber Congress / WCC) መረጃ በማሰራጨት እገዛቸው እንደሚያስፈልጋቸውም ጨምረው ገልጸዋል፡፡

አቶ ተፈሪም በበኩላቸው፣ የቢዝነስ ዲፕሎማሲ ዳይሬክቶሬት ጄኔራሉ ምክር ቤቱ በኢትዮጵያና በቻይና ጓንዡ ግዛት መካከል ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የሚያደርገውን ጥረት ይበልጥ ለማሳደግ አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ እንደሚሠራ እምነታቸውን ገልጸዋል፡፡ ለዚህም በሽርክና መሥራት የሚፈልጉ የግዛቲቱን ባለሀብቶች በመመልመል ከሀገር ውስጥ ኩባንያዎች ጋር የሚሠሩበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እንደሚተባበርም ቃል ገብተዋል፡፡

በመጨረሻም፣ 4ኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ላይ ትኩረት አድርገው መሥራት እንደሚያስፈልግም ተወያይተዋል፡፡

# የቻይና የግንባታ ቁሳቁሶች ኩባንያ የምክር ቤቱ አባል ለመሆን ጠየቀ



ከላይ ከቀኝ ወደ ግራ፡- አቶ እንዳልካቸው ስሜ እና ሚ/ር ኤሪክ ዩ

በምህፃረ ቃሉ ‹‹ሲ.ኤን.ቢ.ኤም›› በመባል የሚታወቀው የቻይና ብሄራዊ የግንባታ ቁሳቁሶችና መሣሪያዎች አስመጪና ላኪ ኮርፖሬሽን (China National Building Materials & Equipment Import and Export Corporation /CNBM) ከኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አባል ኩባንያዎች ጋር በትብብር መሥራት እንደሚፈልግ በተወካዩ አማካኝነት ገለጸ፡፡ ኮርፖሬሽኑ የምክር ቤቱ አባል መሆን እንደሚፈልግም ፍላጎቱን አሳይቷል፡፡

ታህሣሥ 27 ቀን 2010 ዓ.ም. የኮርፖሬሽኑን ተወካይ ሚ/ር ኤሪክ ዩን በጽ/ቤታቸው ተቀብለው ያነጋገሩት የምክር ቤቱ ዋና ፀሀፊ አቶ እንዳልካቸው ስሜ የኮርፖሬሽኑን የትብብርና የአባልነት ፍላጎት መቀበላቸውን ከተወካዩ ጋር ባደረጉት ውይይት ላይ ገልጸዋል፡፡ ኮርፖሬሽኑ በኢትዮጵያ የተመዘገበ ኩባንያ እስከሆነ ድረስ ህግና ደንቡ የሚፈቅደውን ቅድመ ሁኔታ በማሟላት በተመዘገበበት ከተማ የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አባል መሆን እንደሚችል ገልጸዋል፡፡ የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አባላት የክልል ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች፣ የሁለቱ የከተማ (አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ) ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች እንዲሁም ሀገራዊው የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እና ስድስት የዘርፍ ማኅበራት እንደሆኑና የከተማ ምክር ቤቶች የተለያዩ ዘርፎችን በአባልነት እንደሚይዙ ይታወቃል፡፡

ሲ.ኤን.ቢ.ኤም. በግንባታ ዙሪያ የሚሠራ ኩባንያ እንደመሆኑ በቀጣይ በጋራ የሚሠሩ በርካታ ሥራዎች መኖራቸውን የገለጹት ዋና ጸሐፊው፣ ምክር ቤቱ አሁን ካለው የምክር ቤቱ ዋና መ/ቤት ጀርባ ባለው ክፍት ቦታ ላይ አዲስና ዘመናዊ ህንፃ ማስገንባት እና እጅግ ዘመናዊና ዘርፈ ብዙ አገልግሎት የሚሰጥ ግዙፍ ማዕከል ለማሠራት ፕሮጀክት ቀርጾ በመንቀሳቀስ ላይ መሆኑን ጠቅሰው በቁሳቁስ አቅርቦትም ሆነ ሌሎች የግንባታ ሥራዎች ሁለቱ ተቋማት በአጋርነት መሥራት የሚችሉበት ዕድል መኖሩን በውይይታቸው ላይ አንስተዋል፡፡

በምክር ቤቱ አዘጋጅነት በያመቱ ህዳር ወር ላይ በሚደረገው ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒትና በያመቱ ግንቦት ወር ላይ በሚካሄደው የኢትዮጵያ የቢዝነስ ሩጫ ላይ በመሳተፍ ምርትና አገልግሎቱን ማስተዋወቅ ይችላል የሚለውም የውይይቱ አካል ነበር፡፡

ሲ.ኤን.ቢ.ኤን. በቻይና የግንባታ ቁሳቁሶች ኢንዱስትሪ በዓለማችን ትልቁ የቻይና መንግሥት የሲሚንቶ አምራች ኩባንያ ሲሆን በኢትዮጵያ ገበያ ውስጥ በሲሚንቶና ተያያዥ ፋብሪካዎች ግንባታ ጠቅላላ ተቋራጭነት እና የግንባታ ዕድሳትና ማሻሻል፣ የንፁህ ውሃ ፕሮጀክት፣ የቢራና መጠጦች ማቀነባበሪያና ማሸግ ላይ ከአሥር ዓመታት በላይ የቆየ መሆኑም ተገልጿል፡፡

# የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የግልግል ማዕከል

## ማዕከሉ

- በአዋጅ ቁጥር 341/95 አንቀጽ 5(6) በምክር ቤቱ 10ኛ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሠረት መቋቋሙ፣
- የማቋቋሚያ ደንብ እና የግልግል ሥርዓቱ የሚመራበት የግልግል ደንብ የተዘጋጀለት መሆኑ፣
- የማቋቋሚያውም ሆነ የግልግል ደንቡ በጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሠረት የፀደቀ መሆኑ፣ በንግድ ማኅበረሰቡ መካከል የሚፈጠሩ ንግድ ነክ አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚያስችል ምቹ መደላድል ተፈጥሯል፡፡ በተለይም፣

  ⇒ የጉዳዮችን ሚስጢራዊነት ለመጠበቅ እና በአጭር ጊዜ ውስጥ ፍትሃዊ ውሳኔ ለመስጠት በሚያስችል መልኩ የተቋቋመው የግልግል ማዕከል ከንግድ ማኅበረሰቡ በተለያዩ ጊዜያት ወኪሉ በሆነው የሀገር አቀፍ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ለመዳኘት ሲነሱ የነበሩ ጥያቄዎችን ትርጉም ባለው መልኩ የሚመልስ ይሆናል፡፡

## ማዕከሉ በዋነኛነት የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል

- አለመግባባቶች በግልግል ወይንም በሌሎች አማራጭ የግጭት መፍቻ መንገዶች እንዲፈቱ ለማድረግ የሚያስችል መድረክ ያመቻቻል፡፡
- በግልግልና ሌሎች አማራጭ የግጭት መፍቻ መንገዶች ዙሪያ በብዙሃን መገናኛ በማስተማር፣ ትምህርታዊ ውይይቶችን በማድረግና የተለያዩ ዐውደ ጥናቶችን በማካሄድ ኅብረተሰቡ የሚማርበትን ዕድል ያስፋፋል፡፡
- የንግድ አለመግባባቶች በግልግል እንዲቋጩ ለማድረግ በሀገር ውስጥ የግልግል ዳኝነትን ያበረታታል፡፡
- አለመግባባቶች በግልግል ወይንም በሌሎች አማራጭ የግጭት መፍቻ መንገዶች እንዲፈቱ ያስተምራል፣ ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ የግልግል ጉዳዮች የሚስተናገዱበትን መድረክ ያመቻቻል፤ ለዚህ ተግባርም አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡
- በግልግልና በአማራጭ የግጭት መፍቻ መንገዶች ላይ ያተኮሩ ጥናትና ምርምሮችን እንዲደረጉ ያበረታታል፡፡

## FDRE MoFA's Representative in Guizhou Province, China Pays Courtesy Visit

Endalikachew Semie, Secretary General of The Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA), received on December 26, 2017 at his office Mr. Teferi Melesse, FDRE Ministry of Foreign Affairs (MoFA), Business Diplomacy Director General in Guizhou Province in China who made a courtesy visit to ECCSA before his departure. In the meantime, the officials discussed on mutual activities ECCSA and MoFA would cooperate.



Top right to left: Endalkachew Sime and Teferi Melesse

The Secretary General expressed his feeling if the two sides work together in facilitating the provision of up-to-date information in the promotion of trade and investment activities undertaken between the two sides recommending that exchange of information should be as timely as possible.

Endalkachew also urged Teferi to make his effort to communicate Chinese investors, who would be interested to cooperate in the Chamber Hub development project, the biggest ever project proposed by the Chamber. There is also a need to promote the Ethio-Chamber International Trade Fair that is conducted annually and the various publications of ECCSA so that Chinese investors and companies should be addressed, the Secretary General added.

Recalling that Ethiopia was designated to host the 12th World Chamber Congress (WCC) in 2021, Endalkachew also requested for cooperation in disseminating information.

The Director General, Teferi, on his part said that his Directorate works to the best it could be to strengthen the trade and investment relation between the two sides. He also promised his Directorate would work in identifying Chinese companies that would be interested to work in joint venture.

Finally, the two sides talked on the ways they should work on 4th industrial revolution with more emphasis.

## CNBM - Rummages for Membership in ECCSA



Top right –left: Ato Endalkachew Sime & Mr. Eric Yu

Endalikachew Semie, Secretary General (S.G.) of The Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA), received on January 5, 2018 at his office Eric Yu, Representative of China National Building Materials & Equipment Import and Export Corporation (CNBM). The purpose of Mr. Yu's visit was to introduce CNBM and seek for cooperation with ECCSA.

Endalkachew, who provided the delegation with a short briefing about the overall activities of ECCSA, warmly welcomed and hosted CNBM's cooperation interest. Recalling that ECCSA has big project initiated to construct a new and comprehensive building at the rear of the old one, and is pursuing the construction of Chamber Hub and there is a need for materializing the projects, the S.G. expressed there is an open room for CNBM to use the opportunity to work in partner with ECCSA.

He also forwarded his pleasant invitation if CNBM would be able to participate in the Ethiopian Business Run that is conducted every May and exhibit its products in the Ethio-Chamber International Trade Fair that is conducted every November.

Mr. Yu also expressed the interest of his Corporation to be member of ECCSA and the S.G. positively hosted the matter as long as CNBM is a registered company in Ethiopia. Accordingly, it was recommended that the Corporation would be able to begin to lodge legal credentials with all the necessary formalities to Addis Ababa Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ACCSA). It is noted that ECCSA is an apex chamber whose members are the regional chambers of commerce and sectoral associations, the two city chambers of commerce and sectoral associations (Addis Ababa and Diredawa) that comprise individual firms (sectors) as their members and the national chamber of sectoral associations along with six sectoral associations.

CNBM, the largest state-owned group in Chinese building materials industry and the largest cement manufacturer in the world, has been in Ethiopian market over ten years dealing as general contractor for Cement Plants, Glass Plants, Gypsum Plants as well as Plant Modification and Upgrading, Water Treatment System, Waste Power Generation Project, Beer and Beverage Processing Plants and Package Plants.

Mr. Yu said CNBM is the one designed and constructed Derba MIDROC Cement, and right now, it is running the National Cement, Mugher Cement, and Derba Cement.